**የኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ**

**በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ፣ ካለፈው የቀጠለ**

**ክፍል ፵፱ የመጨረሻ ኑዛዜ፣**

እንዴትና በምን መንገድ ለመጨረሻ ኑዛዜ እንደደረስኩ ለመግለፅ ብቸገርም ለምን ለዚህ እንደበቃሁ ማሳወቁን እንደ ግዴታየ ቆጥሬዋለሁ። እንደምታውቁት ተቸግሬያለሁ። ሆኖም ህይወቴ ከመቸውም በበለጠ ከባድና ውስብስብ ችግር ላይ ወድቋል። ለአንድ ነፍስ ማሰብ፣ በአንድ ነፍስ መቁረጥ ቀላል እንደነበር ያወቅኩት አሁን ነው። እንደምታውቁት ከደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ ትምህርት አቋርጠን በአረመኔው የኦሮሞ ቄሮ ታፍነን ከተወሰድን 507 ቀን ወይም 1 ዓመት ከ 4 ወር ከ 27 ቀን ሆኖናል። የታፈኑት የትምህርት ቤት ጓደኞቸ ዛሬም የት እንደደረሱ አላውቅም። በወለጋ በተለይ እዚህ እኔ ያለሁበት አካባቢ የሰው ልጅ በግፍ መገደሉ እንደቀጠለ ነው። እኔን አስጠግተው፣ አባት ሆነው እስከአሁን ያቆዩኝ አባት አባ ዳዲ በኦሮሞ ልዩ ኃይል በጥይት ተመተው ሆስፒታል ገብተዋል። ልጃቸው ጫልቱም ታስራለች።

አባ ዳዲ በጥይት የተመቱበት ምክንያት ደግሞ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ አባል ስለሆኑና ቤተክርስቲያኑን ታጣቂዎች ስለወረሩት ቤተክርስቲያኑን አትድፈሩ ለቃችሁ ውጡ በማለታቸው ነበር። አባ ዳዲ በህይወት ተረፉ እንጅ ሁለቱ የሰበካ ጉባዔ አባላት ወዲያው ህይወታቸው አልፏል። ሁለት ገድለው አባዳዲን ያቆሰሉት ደግሞ ወራሪዎቹ ሳይሆኑ ትክክኛ ፍርድ ይሰጣሉ ተብለው ከተጠሩት ልዩ ኃይል አባላት አንዱ መሆኑ ነገሩን አወሳሰቦታል። ልጃቸው ጫልቱ የሆነውን ስታይ የአባቷን ጠበንጃ ይዛ ወጥታ ገዳዩን የልዩ ኃይል አባል ገደለችው። በዚህ ምክንያት እሷ ወደእስር ቤት ተወረወረች። ጫልቱ ባለቤቷ አስር አለቃ ዲማ ገለታን የገደሉት የኦሮሞ ታጣቂዎች ነበሩ። ዛሬም አባቷን ሲደግሙባት ራሷን መቆጣጠር አልቻለችም እንጅ ጫልቱ ቅዱስ የምትባል መልካም ሴት ነበረች።

አሁን እኔና እማማ ሌንሳ የጫልቱን ልጆች ኪያና ደበሌን ይዘን በሀዘን ተቆራምደን ባዶ ቤት ቁጭ ብለናል። አባ ዳዲ ጋር ሄጄ ከጎናቸው ውየ አድሬ እንዳላስታምማቸውና ጫልቱን እስር ቤት ሄጀ እንዳልጠይቅ እማማ ሌንሳ ከልክለውኛል። እማማ ሌንሳ እንደወጣሽ ይደፉሻል፣ በዚህ ደግሞ አንች ብቻ ሳትሆኝ እኔና ልጆቹም እንጎዳለን ብለው ተማፀኑኝ። ለነገሩ በእማማ ሌንሳ ለመፍረድ ይቸግራል። ምክንያቱም እኔ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ብየ ነው እንጅ ከወጣሁ በሰላም እንደማልመለስ አውቀዋለሁ። በዚያ ላይ  የተወሰነ ቀን ከጫልቱ ጋር ቤተክርስቲያንና ጓደኛዋ ቤት ከመሄድ በቀር ከቤት ወጥቸ ስለማላውቅ አካባቢውን አላውቀውም። ዛሬ በድንገት ድንገት የተበተነውና ሀዘን የገባበት የአባ ዳዲ ቤተሰብ  እኔ በህይወት እንድቆይ ብዙ ደክመዋል። እነሱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ ሰውን በሰውነቱ የሚወዱ ስለሆኑ ለእኔ ያደረጉት መልካም ነገር ሁሉ በደግነትና በችሮታ ነበር። አሁን ግን እማማ ሌንሳ በዚህ ክፉ ቀን እኔንም እንዳያጡ፣ እንደማስፈልጋቸው ጭምር ነግረውኛል። እኔ ደግሞ የክፉ ቀን ዘመዶቼን ባልጠቅማቸውም አብሬያቸው ለመሞት ወስኛለሁ።

እኔ በኦሮሙማ ፓለቲካ ምክንያት ነፃነት አጥቼ አቅመ ቢስና ደካማ ሆንኩ እንጅ፣ በዚህ ሰዓት እማማ ሌንሳ የጎደላቸውን ሁሉ እየሸፈንኩ ባግዛቸው እመኛለሁ። አባ ዳዲን ከጎናቸው ሁኜ ባስታምማቸው ደስ ይለኝ ነበር። ግን ከቤት መውጣት ስለማልችል ምኞቴ አይሳካም። ተሽሏቸው ወደቤታቸው እንዲመለሱ በፀሎቴ አስባቸዋለሁ። ጫልቱንም ተመላልሸ ስንቅ ማቀበል አልችልም። ሆኖም ምኞት አይከለከልምና፤ “አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል” የሚሉት አይነት ቢሆንም፤ ኪያና ደበሌን ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራቸው፣ ሰው መግደል ሀጢያት እንደሆነ እያስተማርኩና ፍቅር እየሰጠሁ እንደልጆቼ ተንከባክቤ በእናታቸው በጫልቱ መንገድ ባሳድጋቸውም እወዳለሁ።

እማማ ሌንሳ ልባቸው በጣም በሀዘን ተሰብሯል። ከአሁን በኋላ ኑሮ እንዴት እንደሚቀጥል የሚታወቅ ነገር የለም።ሕዝቡ ታጣቂውን ስለሚፈራ እንዴት ናችሁ ብሎ ብቅ ያለ ሰው የለም። እኛም ደመወዝ የለን፣ ሌላ ገቢ የለን፣ እርሻ የለን፣ ለጊዜው ቤት ያፈራውን በቁጠባ እየተመገብን ተፋጠን ቁጭ ብለናል። የቀን ጉዳይ ነው እንጂ እኛ ራቡም ጥማቱም ሳይገለን አይቀርም። በእርግጥ ጫልቱ መሳሪያውን ይዛ ስትወጣ ልጆቼን አደራ ብላኛለች ። ጫልቱ ልጆቿ በገዳዮቹ እንዳይጠለፉባት ስጋት አለባት። አሁን ሁሉም ነገር ከቁጥጥሯ ውጪ ሆኗል። ልጆቿ ከተጠለፉ የባለቤቷ ህልም የአባ ዳዲና የእሷ ድካም ሁሉ ከንቱ እንደሚቀር ታውቃለች። እኔ እስከዛሬ የምመኘው ሞቴን ነበር። የባሰ አታምጣ እንዲሉ አሁን ያለአቅሜ ትልቅ አደራ ተቀብያለሁ። የማይሳካ ቢመስለኝም የጫልቱን እናትና ልጆቿን ይዤ ከዚያ ሰውበላ አገር ብወጣ እመኛለሁ። እንግዲህ እናንተም ጫልቱ ተፈትታ እናቷንና ልጆቿን እንድትረከበኝ በፀሎት አትርሱኝ።

በነገራችን ላይ በሰሜን ሸዋ በደረሰው ሁሉ በጣም አዝኛለሁ። ቢሆንም ህዝቡን ከዳር እስከዳር ስላንቀሳቀሰው ደስ ብሎኛል። አማራ ቆርጦ ከተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም መኖር ይችላል የሚለው ተስፋየና ምኞቴ እውን እንደሚሆን ተሰምቶኛል። አማራ ከኦሮሙማ ጭፍጨፋ ነፃ ሲወጣ እኔ በህይወት ቆይቸ ድሉን ላላይ እችላለሁ። እናንተ ግ ን ተስፋ እንዳትቆርጡ አደራ እላለሁ። ነፃነታችሁን በእምቢተኝነት እንደምትጎናፀፉ ግን ተስፋ አለኝ።

በአማራ ክልል በየከተሞቹ ስለነበረው ሰልፍ የታዘብኩትን ላካፍላችሁ። የሰልፉን ሂደት ሳየው የአማራ ህዝብ የሞራል ልዕልና ከአብይ አህመድ ኦዴፓ/ኦነግ ጀሌ ጋር ሲወዳደር ልዩነቱ የትየለሌ ነው። የኦሮሙማው መንግሥት አንድ ምኒሊክ የፈረስ ሌባ ነው የሚል ድፋርና ከእውቀት ነፃ የሆነ ዘፋኝ ሀጫሉ ሞተ ብለው እንዴት እንዳዘኑ አይተናል። ሀጫሉ በወጣትነቱ በእነሱ የሴራ ፓለቲካ መሞቱ እንደማንኛውም ሰው ያሳዝናል። ነገር ግን ጥልቅ ሀዘናቸውን የገለፁበት መንገድ በርካታ ከተሞችን በማውደም፣ ከግድያው ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን ህዝብ በጅምላ በማረድ፣ አስከሬን በመቆራረጥና በመጎተት ነበር። ተረኛው የአብይ መንግሥትም የሀጫሉን በየኢምባሲው ገንዘብ በመሰብሰብ፣ ሀዘን ሚዲያ በማጣበብ፣ ሲያደነቁረን ከመክረሙም በላይ፣ ሀውልት በማሰራት፣ መንገድ በመሰየም፣ ለቤተሰቦቹ ከአምቦ ጠርቶ አዲስ አበባ የቤት ቁልፍ በማስረከብ ይሉኝታ ቢስነታቸውን አሳይተዋል።

በአንፃሩ በመተከል፣ በወለጋ፣ በአጣየ፣ በካራቆሬ፣ በከሚሴ፣ ወዘተ በግፍ የተጨፈጨፈው አማራና የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት የሀጫሉን ያህል ሚዛን ስለማይደፉ፣ መንግስትም ሚዲያውም ፀጥ ረጭ በለዋል። በደቡብም በኦሮሙማ ትንኮሳ የሚገደሉት ሰዎች ደመከልብ ሆነው እየቀሩ ነው። ያስደሰተኝና ተስፋ የሰጠኝ የአማራ ህዝብ ደግሞ፣ ይኸ ሁሉ በደልና ሀዘን እያለበት አንድም አማራ ቆጨራና ሜንጫ ሳይዝ፣ በጎኑ ያለውን የሌላ ነገድ ተወላጅ ሳይተናኮል፣ መኪናና ቤት ሳያቃጥል፣ ገዳዩን የአብይ አህመድን ኦሮሙማ ሼኔና አስገዳዩን የአብይ ሎሌ አዴፓን ብቻ አውግዞ በተደጋጋሚ በሰላም ሲበተን ማየቴ ነው።

አብይ አህመድ ወደስልጣን ሲመጣ በአለም ላይ ያለን አማሮች ሁሉ በደስታ፣ በድጋፍ ሰልፍና በፍቅር ተቀብለነው ነበር። እሱ ግን ከሀዲ፣ ቃለ አባይና መሰሪ በመሆኑ፣ ደማችን በ 27 ዓመት በወያኔ አገዛዝ ከፈሰሰው ደም እጥፍ ድርብ ሁኖ እንደ ጅረት እንዲፈስ እያደረገ ነው። ወገኖቼ ሆይ ትግላችሁን አጠናክራችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል። አብይ አህመድ እንኳን ተቃውማችሁት፣ አውቀንብሀል፣ አንፈልግህም ብላችሁትና ትክክለኛ ማንነቱን አደባባይ አስጥታችሁበት ቀርቶ እንወድሀለን፣ መሪያችን ነህ፣ በተባለም ጊዜ ሊያጠፋችሁ ስለወሰነ የበቀል ክንዱን ከማንሳቱ በፊት፤ በቁጭት እንደወጣችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል። ሞት፣ መፈናቀል፣ መደፈር፣ መታፈን፣ መቃጠል፣ በቃን ። አትግደሉን ማለት ተፈጥሯዊ ነው። አዴፓም ለአማራ ህዝብ ደንታ ቢስ እንደሆነ የምናውቀው ነው። የአማራ አንገት ሲቆረጥ፣ ማህፀን ውስጥ ያለ ፅንስ ማህፀን እየተቀረደደ ሲጣል ጥቃቱ አልተሰማቸውም። ዛሬ በባህርዳር ሰላማዊ ሰልፍ የብልፅግና ባነር ተቀደደ ብለው ብስጭትም፣ ቁጣም አሳይተው መግለጫ እስከማውጣት ደርሰዋል። ከአማራ ህዝብ ጭፍጨፋ ባነሩ ለአዴፓ የበለጠ ዋጋ አለው። በዚያ

ላይ የሎሌ ነገር ሆኖባቸው አብይ ስለተወገዘ ሀፍረት ተሰምቷቸዋል። ስለዚህ እኛ የአማራ ልጆች መሪ እንደሌለን አውቃችሁ የቀደሙት ወላጆቻችን መሪ ቃል "ያለመስዋዕትነት ድል የለም!" "ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነፃነት!" የሚለውን በተግባር እንደምታውሉት አልጠራጠርም።

በተረፈየኢትዮጵያ ሕዝብ ከአማራ ጎን ሊቆም ይገባል፣ እላለሁ። የቀን ጉዳይ ነው እንጅ የአብይ ገዳይ ቡድን አማራን ካዳከመ በኋላ ወደሌላው ነገድ እንደሚዞር አዋቂ መሆንን የማይጠይቅ ሀቅ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት እንኮራለን የምትሉ፣ ምሁራን፣ አርቲስቶች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ እንዲሁም ሰርቆም፣ ሰርቶ በላቡም፣ አጎብድዶም የከበረ ነጋዴ ሁሉ፣ የሕዝቡን ትግል በመቀላቀል አገራችሁን ከጥፋት ታድጋችሁ ታሪክ እንደምትሰሩ ተስፋ አደርጋለሁ። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ በግፍ ለሚጠፋው አማራ አጋርነትን ማሳየት ይጠበቅባችኋል።

ዛሬ የመጨረሻ ኑዛዜ ያልኩበት ምክን ያት በድጋሚ ለመፃፍ ስለማልችል ነው። እስከዛሬ አባ ዳዲ የወቅቱን ሁኔታ እንድከታተል ያደርጉ ነበር። አሁን እሳቸው ይሄን ማድረግ አይችሉም። ከአሁን በኋላ በኢንተርኔት ለመጠቀም አልችልም። አሁን ያለኝ ሂሳብ ከሰዓታት በኋላ አያስጠቅመኝም። የሕዝባዊ እንቢተኝነቱ ወደነፃነት እንደሚወስዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። በነፃነት ጊዜ በኦሮሙማ ፓለቲካ የደምቢ ዶሎ ተማሪዎች መታፈንና እንደወጡ መቅረትም በታሪክ ተፅፎ ለትውልድ መማሪያ ይሆናል። እድለኛ ብሆን በህይወት ቆይቸ የጫልቱን ልጆች በማሳደግ፣ እማማ ሌንሳን በምችለው ሁሉ ባግዛቸው፣ በተለይም የአማራ ህዝብ ነፃ ወጥቶ የኢትዮጵያ ህዝብ በሰላም ሲኖር ማየት ብችል ፈቃዴ ነበር። ነገር ግን ለዚያ የምበቃበት አጋጣሚ የተመቻቸልኝ አይደለሁም። ድልና ነፃነትን እመኝላችኋለሁ።

ተፈፀመ

ዘውዲቱ የማነ

2021-04-23